# ኢህአዴግና ተቃዋሚዎቸ ምንና ምን ናቸው

**ዮናስ 09-24-14**

*ይህ ፅሁፍ ተቃዋሚዎች ከመድበለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ስርአት፣ ከልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታና ከሰብአዊ መብቶች አንጻር ኢህአዴግ ላይ ለተነሱ ማመሃኛ ክሶች መልስ የሚሰጥ ነው፡፡*

*የፖለቲካ ፓርቲዎች በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ላይ የላቀ ሚና መጫወት እንደሚችሉ እና መጫወትም እንደሚገባቸው ኢህአዴግ በተደጋጋሚ መናገሩንና በተግባርም እየሰራ መሆኑን መካድ አይቻልም፡፡*

*የአንድን የህብረተሰብ ክፍል መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያሥችሉ አማራጭ ሃሳቦችን በማመንጨት፣ እነዚህ ሃሳቦች በህብረተሰብ ክፍሉም ሆነ በአጠቃላይ በህዝቡ ተቀባይነት እንዲያገኙ በመጣር፣ ሃሳቦቹ በዴሞክራሲያዊ አኳኋን ተግባራዊ እንዲሆኑ በመታገል ከፍተኛ የአመራር ሚና መጫወት ይችላሉ። በዚህ መልኩ የተደራጀ አመራር ሰጥተው የህዝብን ድጋፍ ካገኙ የመንግስት ሥልጣንን ይዘው ሃሳባቸውን ተግባራዊ በማድረግ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ውስጥ ከፍተኛ አሥተዋፅኦ እንደሚያበረክቱ ድርጅቱ ስለመቀበሉ በድርጅታዊ ሰነዶቹ ላይ በግልጽ የተመለከተ ከመሆኑም አልፎ በተግባርም ተቃዋሚዎቹ በዚሁ አለም አቀፍ ተቀባይነትን ባገኘው መርህ እንዲመሩ የሚጠበቅበትን ሁሉ መስራቱም የሚካድ አይደለም፡፡*

*ነገር ግን 'ፓርቲዎች በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ላይ የሚጠበቅባቸውን ሚና ለመጫወት የሚችሉት አመለካከታቸው ፣እምነታቸውና አሠራራቸው ዴሞክራሲያዊ ሲሆን ነው' የሚለው ገዢው ፓርቲ፤ የውስጥ አሰራሩ ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ ፓርቲ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባትና ማበብ ፋይዳ ያለው አስተዋፅኦ ማበርከት አይችልም ሲል አፅንኦት የሚሰጠው ይኸው ከሳሾቹ ከሰሞኑ የገጠማቸውን ችግር አስቀድሞ በመረዳት ነው፡፡*

ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ወሳኝ አስተዋፅኦ እንዳለውና ተቋዋሚ ፓርቲዎችም ሁሌ የውዝግባቸው አንድ ምክንያት አድርገው የሚያቀርቡትን የሚዲያ አጠቃቀም በተመለከተም ገዢው ፓርቲ አገሪቱ በምትከተላቸው መሠረታዊ አቅጣጫዎች ላይ ተከታታይ ትንተናዎችና በተለያዩ ወገኖች የሚቀርቡ የተለያዩ አማራጭ ሃሳቦችን እያቀረበ የውይይትና የክርክር መድረክ ሆኖ ማገልገል እንዳለበት በግልፅ አስቀመጧል። ሚዲያው ይህን የመሠለ በሳል የፖለቲካ ውይይትና ክርክር መድረክ ሆኖ በሚያገለግልበት ወቅት ሃሳቦችን በነፃ በማንሸራሸር የዴሞክራሲ ባህል እንዲያብብ የሚረዳ መሆኑን በፅኑ አሥምሮበታል፡፡ ከዚህ ውጪ የሆነ የሚዲያ አጠቃቀም ደግሞ ከመርህም ሆነ ከህግ ተጠየቅ ውጪ ይሆናል ማለት ነው፡፡

በዚሁ መሠረት የአገራችን ፖለቲካ በድርድርና በውይይት የሚመራበትን ባህል ለማዳበርና የጥላቻና የአመፅ ፖለቲካ ቦታ እንዳይኖረው የሚያደርግ ህብረተሰባዊ ግንዛቤ በመፍጠር ረገድ የበኩሉን ድርጅታዊና መንግስታዊ ሚና እንደተጫወተ  የሚገልፀው ኢህአዴግ፣ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሠጥቶ በመቀበል ዴሞክራሲያው ድርድርና ውይይት የሚመራና እየተመራ ያለመሆኑ ግን ትልቁ እንቅፋት እንደሆነ አስቀድሞ ተናግሯል። ይኸው ሊያውም በምርጫ ዋዜማ ላይ በምንገኝበት በዚህ ሰአት ከላይ ኢህአዴግ በገለጸው ምክንያት ተቃዋሚዎቹ እየታመሱ መሆኑን ያጤኗል፡፡

ብዙ ጊዜ በአንዳንድ ተቃዊሚዎች በኩል በተለይ የውስጥ መታመሳቸውን በኢህአዴግ ላይ በማላከክ የሚታወቁቱ ሰማያዊ፣ አንድነት፣ መኢአድና መድረክ በአገራችን የተከናወኑ ምርጫዎችን ነፃና ፍትሃዊ ላለማድረግ በምሳሌነት የሚያቀርቡት ምርጫ 97 እስከ ድምጽ አሠጣጡ ድረስ የነበረው ሂደት ድፍን ዓለም ያደነቀው ነፃ፣ፍታሃዊና ዴሞክራሲያዊ እንደነበ ኢህአዴግ ያወሳል። ኢህአዴግ 'ከድምፅ አሰጣጡ ሂደት በኋላ የተከሰቱ መደማመጥና መነጋገር የጎደላቸው የሁከትና የአመፅ አካሄዶች የፈጠሩት ነውጥና ማህበራዊ መታወክ ምንጫቸው የጥላቻና የአመፅ ፅንፈኝነት ናቸው' ሲል ሲያቀርብ የነበረው መከራከሪያም ይኸው በገዛ ቤታቸው በተግባር እየታየ መሆኑ አስቀድሞም በስርአቱ ላይ ሲያቀርቡ የነበሩት ክሶች መሰረተ ቢስ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

እነዚሁ የጥላቻና የአመፅ ፅንፈኝነት ጎራ ውስጥ የሚመደቡት ተቃዋሚ ፓርቲዎች የፖለቲካ ምህዳርን በተመለከተ የሚያነሱት ጥያቄ ፍፁም መሰረተቢስና ውሃ የማያነሳ ጥያቄ መሆኑን፤ ጥያቄውም 'ከሽግግሩ ወቅት ቻርተር ጀምሮ የተመለሰ ጥያቄ ነው' የሚለው

ኢህአዴግ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ በመጠቀም እየተበራከቱ መምጣታቸውን፣ በርካታ ድምፆችና ሚዲያዎች መፈጠራቸውን፣ የተለያዩ የግል ፕሬሶች መፍላታቸውን፣ የፖለቲካ ምህዳሩ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በነፃነት ነገር ግን ህጋዊ በሆነ መንገድ እንዲጓዝ ህጋዊ መሠረት መጣሉን፣ የተቃዋሚዎች የመደመጥ መብትና በምክር ቤት ያላቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ የተካሄደውን የህግ ቀረፃና የማፅደቅ ሂደቶች፣ ከዚህም በላይ ደግሞ የፖለቲካ ምህዳሩ በህጋዊ መንገድ ለሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የፖለቲካ ተዋናዮች የፈጠረውን ህጋዊ መደላድልና አመቺነት /የፓርላማ ህግ፣ የፓርቲዎች የምርጫ ማስፈፀሚያ ህግ፣ የጋራም/ቤት መቋቋም/ የመሳሰሉትን በማስታወስ በምህዳር ጉዳይ ላይ የሚነሳው ሁሉ መነሻውና ምንጩ ሌላና ፀረ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ስለ መሆኑም ኢህአዴግ ደረቱን ነፍቶ መናገሩ ትክክል እንደሆነም ይኸው በተለየ ከላይ በተገለጹት ተቃዋሚዎች ቤት ከተነሳው እሳት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በህዳሴው ዋዜማ ላይ ያለውን ሥርዓት በምርጫ ዋዜማ ላይ ሁሌም ከማወክና ከማወዛገብ የማይቦዝነው የተቃዋሚዎቸ የቁዘማ ፖለቲካ ካምፕ ጊዜ ባለፈበት የአመፅና የጥላቻ ፖለቲካ የሚመራና ሃላፊነት የማይሰማቸው ግለሰቦች ሥብሥብ ነው የሚለው ኢህአዴግ፤ ተቃዋሚዎቹ ሰሞኑን በገቡበት ማጥ ከመረጋገጡም ባሻገር የኢህአዴግን የፖለቲካ ብስለትና ድርጅታዊ ቁርጠኝነት የሚያረጋግጥ ነው፡፡

በተደጋጋሚ በስርአቱም በኩል ሆነ በፖለቲካ ልሂቃኑ በኩል እንደገለጸው  በሃገራችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የተወገደውን የደርግ ሥርዓት ተከትሎ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሚደረገው ርብርብ በየደረጃው የቀጠለ ቢሆንም፤ የዴሞክራሲ ተቋሚት የሚባሉቱ ድርጅቶችም ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ከእለት እለት እየተጠናከሩና የበለጠውኑ እየሠሩ ያሉበት ሁኔታ ቢኖርም፤ በሃገራችን የሚገኙ የተቃዋሚ ፓርቲዎችና ሚዲያው በተለይም ምርጫ በደረሰ ቁጥር ልክ እንደመሥቀል ወፍ የተለመደና ጸረ ዴሞክራሚያዊ የሆነ አካሄዳቸውን ለማለዘብና ወደትክክለኛውና ለሃገራችን እድገት ወደሚጠቅመው መሥመር መመለሥ አለመቻላቸው ሳያንስ ወደለየለት መናከስ ውስጥ ገብተው መገኘታቸውም የሚያሳየን በኢህአዴግ ላይ ሲያቀርቡ የነበረው ክስ የእናቴ መቀነት ጠለፈኝ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

እንግዲህ 'የትኛው ነው ትክክል?' የሚለውን እና ኢህአዴግ ላይ ሲቀርብ የነበረውን ክስ ለመመዘንና አንዳች የራሳችን ዳኝነት ላይ ለመድረስ ምርጫ 97ን እና ምርጫ 2002 ላይ

የነበሩ ሁነቶችን በጥቂቱ ማንሳት ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ እነዚህ በቁዘማ ላይ የሚገኙት ተቃዋሚ ፓርቲዎች በ97 እና 2002 ምርጫ ላይ የነበሩት ቅንጅት፣ ህብረትና መድረክ ፍንክትካች ናቸውና፡፡

በተለይም እንደ ገገሮው ፓርቲ የተቃዋሚዎቹ ጎራ እና ከነዚሁ ጎን የተሰለፉቱ ፕሬሶች በምርጫ 97 ያሳዩት የፖለቲካ ውሥልትና ጎልቶ የተሥተዋለው ከምርጫው በኋላ እንደሆነ ሲወሳ በምርጫ 2002 ደግሞ የአመፅን መንገድ የጀመሩት ገና ከዋዜማው እንደሆነም ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም ድህረ ምርጫ 97ን እና ቅድመ ምርጫ 2002ን በጥቂቱ በማንሳት አሁን ደግሞ በምርጫ 2007 ዋዜማ ላይ ያለውን የህጻሴ ጉዞ ከተቃዋሚዎቹ ውዝግብ አኳያ እንመለከታለን፡፡

በሦሥተኛው አገራዊ ምርጫ ፉክክሩ፣ የድምፅ መሥጠትና የቆጠራ ሂደት ሁሉም በሠላም መጠናቀቁን ተከትሎ አሸናፊው ወገን ቢለይም ተቃዋሚው ሃይል በተለይም ቅንጅትና ህብረት አሁን ደግሞ ከመታመሳቸው አስቀድሞ ሰማያዊ መኢአድና አንድነት ግና የ2007ቱ ምርጫ ፊሽካ ሳይነፋ ለማወክ እና ምርጫው ላይ ህዝቡ አመኔታ እንዳይኖረው ለመስራት ቋምጠው የነበረ ሲሆን ከራሳቸው ውስጠ ዴሞክራሲያዊ እጦት በነበር ሊቀር ችሏል፡፡

ውጤቱን በተመለከተ ሃላፊነትና ሥልጣን የተሰጠው አካል ባደረገው የማጣራት ስራ (በገገሮውም ሆነ በተቃዋሚው በኩል የቀረቡ ታዛቢዎችን በማካተት) የተቃዋሚዎቹ የአሸንፈናል አዋጅ ተገቢነት እንደሌለውና ጥቂት በሚባሉ ቦታዎች ላይ ደግሞ ምርጫ እንዲደገም በመወሰኑ ቀድሞውኑም ቢሆን በአቋራጭ ሥልጣን የቋመጠው ሃይል ለህግ አልገዛም ባይነቱን እንዴት ቀጥሎበት እንደነበር አይረሳም፡፡

እነዚህ አሁን በመድረክ ጥላ ሥር የሚገኙትና የቤት ስራቸውን ሳይጨርሱ ለመዋሃድ ቋምጠው በነበር የቀሩት መኢአድ፣ አንድነትና ሰማያዊ፣ በ3ኛው ምርጫ ክፍለ ጊዜ በቅንጅትና በህብረት ሥር ሆነው በወቅቱ በያዙት የዜሮ ድምር ፖለቲካ ቀጥለው አመፅ በመቀስቀስ ወደሥልጣን ለመምጣት ያላቸውን ውጥን እውን ለማድረግ፣ በቀን ቢያንሥ ከሦሥት ጊዜ በላይ የፕሬስ መግለጫ በመስጠት አመፁን ለማጋጋል ያላሰለሰ ጥረት ማድረጋቸውንም አንዘነጋም ፡፡

ይህንኑም የወቅቱ የኢህአዴግ የምርጫ ኮሚቴ ሰብሳቢ በሁለት ምርጫ ወጋቸው ላይ እንዲህ ሲሉ ይገልፁታል፡፡ "አብዶ ማሳበድ የሚያውቀው የኢትዮጵያ የግል ፕሬስ የቅንጅትን የጢትና ማታ መግለጫዎች በሰፊው ያራግባል፡፡" ሲሉ በሁለት ምርጫ ወጋቸው አውግተውናል፡፡ ከዚህ በመነሳት  የግል ፕሬሱና ተቃዋሚው ድህረ ምርጫ 97 ከህግ የበላይነት በላይ በመሆን ህግንና ህገወጥነትን በማጣቀስ የተቋማትን ህጋዊና ሉአላዊ ስልጣን ከመጋፋት ጀምሮ፣ ገዢው ፓርቲንም ሆነ መንግሥትን፣ አልፎም የባለሥልጣናትን የግል ጉዳይ ሳይቀር በማንሳትና ጮኸው በማጯጯህ ሃገሪቷን ለትርምስና ወንበሩን ለራሳቸው   ቢመኙም በአለም አቀፍ ደረጃ የጥላቻና የአመፅ ፖለቲካ ወደጎን ተገፍቶ የሰለጠነ የውይይትና የድርድር ባህል ወሳኝ ቦታ እየያዘ መምጣቱን በተገነዘበው ህዝብና ባስገነዘበው መንግሥት፣ የጥላቻና የአመፅ ፖለቲካ፣ ምርጫን የአመፅ መሳሪያ ማድረግና በምርጫ ሰበብ ሁከት መቀስቀስ ፀረዴሞክራሲያዊነትና ዘመን ያለፈበት ፌሊጥ መሆኑን በተገነዘበው ህዝብ አማካኝነት ምኞታቸው ሁሉ  ከሽፎ ጉዞ ወደ ቃሊቲና ወደ ህዳሴ ሆኖ የነበረ ከመሆኑ እንኳን መማር ተስኗቸው በትዝታ እና ቁዘማ ፖለቲካ መናጣቸው ይኸው ለዚህ አበቃቸውና ሲያማሃኙበት የነበረው ኢህአዴግ መናገር ሳይጠበቅበት ነጻነቱን እራሳቸው አወጁ፡፡

የነውጠኛው አመራር በይቅርታ ከተፈታ በኋላ ገሚሱ በይፋ የአሸባሪ ቡድን አደራጅቶ ሲንቀሳቀስ ገሚሱ ደግሞ ላመለጠችው  ወንበር ፋክክር እንደገና ለመፋለም ግንባር ፈጥሮ 'መድረክ' በሚል መለያ ቢንቀሳቀስም ነገሩ ያደቆነ ሰይጣን ሆነና ጨዋታውም ፈርሶ ዳቦውም ተቆርሶ መኢአድ ወአንድነት በአንድ በኩል በሌላ በኩል ደግሞ ሰማያዊ የተሰኘ አዲስ ፋሽን ብቅ ቢልም የትም ሳይደርስ እርሱም  በተመሳሳይ ሲጮህና ሲያጯጩህ የነበረው ባልጨረሰው ጉዳይ ላይ ነበርና በተራው እንዳይነሳ ሆኖ እየተሰባበረ መሆኑ ሁሉ አቀፍ በሆነ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ፍልስፍና እና አተገባበር ላይ ማን ትክክለኛና ቁርጠኛ እንደሆነ አመላክቶናል፡፡ በዚሁ የውግዘትና የአመጽ ፓለቲካ በቅንጅት  ዶቅነው በመድረክ የቀሰሱት ሃይሎች የምርጫ 2007  የመራጮች ምዝገባና ቅስቀሳ ግና በርከት ያሉ ወራት እየቀረው   "ካሸነፍን ትክክል ነው ከተሸነፍን ግን ተጭበርብሯል" የሚል   የትዝታ ፊሽካቸውን ቢነፉም ዞሮ እራሳቸው ላይ ነጠረና አጨነገፋቸው፡፡

የዜሮ ድምር ስብስቡ ከላይ በተገለፀው መልክ ምርጫ 97 ላይ  ቢሸነፍም በተለይም የስብስቡ አደራጅ የሆኑት አንዳንድ አለም አቀፍ ድርጅቶችና በነፃ ፕሬስ ስም የተቋቋሙ

ሃገር በቀል ጋዜጦች ከምርጫ 2002 ወደኋላ 2 ዓመት ቀደም ብለው መድረክ የተባለ ጠንካራና የብዙ ፓርቲዎች ጥምረት የሆነ ፓርቲ መወለዱን በይፋ  ማወጅና ማራገብ ቢጀምሩም፣ መድረክ የተባለው ፓርቲ ከወዴት እነዳለና አመጣጡም ከወዴት እንደሆነ ሳይታወቅ ቢቆይም  በምርጫ 2002 ዋዜማ ላይ የተለመደውንና በምርጫ 97 በዜሮ የተሸነፈበትን የቅንጅት አጀንዳ ይዞ ብቅ ማለቱም የትዝታ ፖለቲካ በገባው መራጩ ህዝብ ለዝረራ ያበቃው ስለመሆኑም በርካታ የፖለቲካ ጠበብቶች በወቅቱ በሰሩት ምርምር ያረጋገጡት ሃቅ ነው፡፡

ሆኖም ይህ ፓርቲና ስብስቡ ልክ እንደ ምርጫ 97ቱ ቅንጅት ቅጥ አምባሩ የጠፋና የሚያስተሳስርና አንድ የሚያደርገው ቀጭን ገመድ እንኳ የሌለው መሆኑ ገና ከመነሻው ግልፅ ነበር፡፡ ይህንንም አቶ በረከት በሁለት ምርጫ ወጋቸው ላይ እነዲህ ይገልፁታል "አንዱ ሶሻል ዴሞክራቲት ነኝ ይላል፡፡ ሌላው ደግሞ ሊበራል ዲሞክራት ነኝ ይላል፡፡ አንዱ የኦሮሞ ህዝብ በቁመቱና በወርዱ ልክ መብቱ አልተከበረለትም ይላል፡፡ ሌላው ኢህአዴግ የሚባል ድርጅት ለብሔር ብሔረሰቦች ከልክ በላይ መብት ሰጥቶ አገሪቱን ሊያፈራርሳት ነው ይላል፡፡አንዱ የሚናገረውን ሌላው ያፈርሰዋል፡፡ ደግሞ እንደገና ሌላው ያፈረሰውን አንዱ ሊገነባ ይውተረተራል፡፡ ከኦሮሚያ ፈልቀናል የሚሉት ዶ/ር መረራ፣ አቶ ቡልቻና ዶ/ር ነጋሶ የሶስት የተለያዩ ደርጅቶች ባለቤት ሆነው ስለመድረክ ጥንካሬ ያወራሉ፡፡ . . ."

ስለሆነም ይህ ሁኔታ በመንግስትና በህዝብ ቁርጠኝነት በቁጥጥር ስር የዋለውን የድህረ ምርጫ 97 አመፅ ለመድገም የተደረገ ሴራ መሆኑን መንግሥት በመገንዘብና እነሱም በዛ ወቅት የጠፋው ሰውና ንብረት መጥፋት የሌለበት መሆኑን በመገንዘብ የጋራና ሁሉንም ተፎካካሪ ፓርቲዎች ሊያግባባ የሚችል የፓለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ስነምግባርና ደንብ ማዘጋጀት እንዳለበት በኢህአዴግ በኩል ጥሪ የቀረበ ሲሆን እንደተፈራውም ሌሎቹ ፓርቲዎች አለም አቀፍ ተሞክሮዎችን እና የሃገራችንን ተጨባጭ ሁኔታዎች በማገናዘብ የስነምግባር ደንብና የምርጫ ስነምግባር ማዘጋጀት ተገቢ እንደሆነ በማመን ወደድርድሩ ገብተው የተስማሙበትን ሰነድ አዘጋጅተው በማፅደቅ ወደሥራ ቢገቡበትም መድረክ የተባለው ፓርቲ ውልደቱ ከቅንጅት በመሆኑ እምቢኝ ባይነቱን ገፋበት፡፡ ያም ሆኖ ግን የመድረኩ መስራችና አፍራሽ እንደሆነ በመድረኩ አባል ፓርቲዎች የተመሰከረለት አንድነት የስነምግባር ደንቡን ከፈረመው መኢአድ ጋር፤ ይልቁንም የብሄር ብሄረሰቦች

መብት ቁቡም ካልሆነው መኢአድ ጋር ግና ለመዋሃድ ሲዘጋጅ አስቀድሞ የከሸፈ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሆኖ ሳለ ለመፎረሻቸው ኢህአዴግ ላይ ማመሃኘታቸው የጸረ ዴሞክራሲያዊነት ደረጃቸው ምን ያህል ፈሩን እንደሳተ ያረጋገጠልን ሃቅ ነው፡፡ ይህ አካሄድ ደግሞ ራሳቸውን በማጋለጥ ብቻ ተመዝኖ የሚቀር አይደለም። ይህ ፀረ ዴሞክራሲያዊና ለሀገራችን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ፋይዳ የሌለው ተራ የፖለቲካ ቁማር ከመሆኑም አንጻር ነው፡፡

በአጠቃላይ በዳበረ የዴሞክራሲ ስርዓት ገዥ የነበረ ፓርቲ ተቃዋሚ፣ ተቃዋሚ የነበረውም ገዢ የመሆኑ ጉዳይ የተለመደና የሚጠበቅ ጉዳይ ነው፡፡ እንደዚህ አይነት የስልጣን ሽግግር ያለአንዳች ችግርና ቀውስ በሰላማዊ መንገድ የሚፈፅም ከመሆኑም ባሻገር ህብረተሰቡ በሚመራባቸው መሰረታዊ አቅጣጫዎች ላይ ይህ ነው የሚባል ለውጥን የሚያስከትል አይሆንም፡፡

ይህ የሚሆነው ግን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ታማኝ ተቃዋሚ በሚል ስያሜ የሚታወቁ የራሳቸው የተለየ ፓሊሲ ከማቅረብ ባሻገር ስርዓቱን የመናድ ሃሳብና ተግባር የሌላቸው ሆነው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡

ተቃዋሚ መሆን ማለት መናድ፣ ማፍረስ፣ በተገኘው አጋጣሚና ባመቸ ስልት በመጠቀም ማደናቀፍ ተደርጎ የሚወሰድበት ሁኔታ እንዲፈጠር እነዚህ ሃይሎች አሁንም እየሰሩ ስለመሆናቸው ከክፍል አንድ ጀምሮ ባየናቸው ሁነቶች ማረጋገጥ ቢቻልም ይኸው የትዝታ አዙሪት ገደል ይዟቸው የሚገባ መሆኑ ይጠበቅ ነበርና የተጠበቀውም ሲሆን ኢህአዴግ ላይ ማላከክ መሰረታዊ ከሆኑ የፖለቲካ ተጠየቆች ጋር መላተም ነው የሚሆነው፡፡

ይህ ብቻ አይደለም በዋናነት ከመንግሥትም ሆነ ከገዢው ፓርቲ የሚጠበቁ ታላላቅ ቁም ነገሮች አንዳሉም ሁኔታውና ጊዜው ያስገነዝበናል፡፡ ይኸውም ምንም እነኳን ብሄራዊ የምርጫ ቦርድ ይህን ሰርቻለሁ ቢልም ገና መጠናከርና የማስፈፀም አቅሙን ማጎልበት የሚጠበቅበት መሆኑን በመረዳት መንግሥት ሰለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ስኬት የበለጠ ትኩረት ሊሰጥ የሚገባው ጊዜ ላይ መሆናችንንም የሚያስገነዝብ ነው፡፡

በህጋዊ መንገድ እየታገሉ ለሚገኙ ፓርቲዎችና የጋራ ም/ቤቱ አካላት ለሆኑትም መንግሥት ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ ሲኖርበት በተለይም የሚዲያና የክርክር መድረኮችን በማሥፋትም የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታውን በማሳለጥ ረገድ ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ማስቻል ይጠበቅበታል፡፡ በጋራ ም/ቤቱ ስምምነት ላይ ስለተደረሰበትና በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ህግ ሆኖ ስለፀደቀው የፓርቲዎች የምርጫ ሥነ ምግባርና ደንብም መንግሥት ብዙ ማለትና ለህዝብ በዝርዝር የማሳወቅ ግዴታውን መወጣትና የጫወታው ሜዳ ለሁሉም እኩል እድል የሚሰጥ መሆኑን በተግባር ማሳየት እንደሚገባው ግን ማስመር ያስፈልጋል፡፡

የሜዳውን ስፋትና ጥበት የሚለካውና ለመምረጥም ሆነ ላለመምረጥ መብት ያለው ህዝብም በተረዳውና በተገነዘበው ህግ ላይ ተመስርቶ ምክንያታዊ እሽታውንና እና እምቢተኝነቱን እነዲገልጽም ይህንኑ የፓርቲዎች ስነምግባርና ህግ ማሳወቅና ይፋ ማድረግ የግድ ይላል፡፡

ከዚያም ሰላማዊውን እና ፀረዴሞክራሲያዊ የሆነውን ሃይል ህዝብ ነጥሎ የማወቅና የአመፅ ሰለባ ከመሆን የሚድንበት እድል ከመፈጠሩም በላይ በቀጣዩ ግንቦት በሚከናወነው 5ኛው ዙር ሃገር አቀፍ ምርጫ ነፃ ፍትሃዊነትና ዴሞክራሲያዊነት ላይ ላቅ ያለ ቀስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡